# የአንታረምም የጥፋት ጉዞ

ዲበኩሉ 01/20/14

አና ጎሜዝ መጣች፣ አና ጎሜዝ ሄደች፣ እንኳን ደህና መጣች፣ እንኳንም ደህና ተመለሰች፡፡ ይህቺ ግለሰብ ትላንት ትርምስ ውስጥ ልትከታት በእጅጉ ጥራ ወደነበረችው ኢትዮጵያ ተመልሳ ስትመጣ እሷ ያለችውና ያሰበችው ሳይሆን ቀርቶ የተረጋጋችና ሙሉ ሰላም ያላትን በልማትም በእድገትም የተሻለች ሀገር በአይኗ ለማየት በመቻሏ ይሄም ትልቅ አጋጣሚ ነው፡፡

አና ጎሜዝ በተቃዋሚው ጎራ ድጋፍና አድናቆትን በገገርው ፓርቲ ወገን ደግሞ የሰላ ተቃውሞን ያስተናገደች ግለሰብ ናት፡፡ አና ጎሜዝ ዲፕሎማት የሆነ ባህናሪ ስብዕና የላትም፡፡ ፓርቹጋላዊቷ እመቤት ለሰው ልጅ ክቡር ሕይወትም እንደ ሰው አክብሮት የሌላት ስለመሆኗ የመለስን ሕልፈት አስመልክቶ የተናገረችውን ማጤን ብቻ ይበቃል፡፡ እናም አና ጎሜዝ በቅርብ ቀን የኢትዮጵያ ጎብኝቷ ከወትሮ ወዳጆቿ ጋር ተገናኝታ መክራለች፡፡ የ97 ዓመተ ምህረቱን የተቃዋሚዎችን ምርጫ የመሩትንና የተሸነፉትን “ጀነራሎችዋን” አነጋግራለች፡፡ ከግሉ ፕሬስ ውስጥም ለቀጣዩ የምርጫ ስራ ተስፋ የተጣለችባቸውን የዘመቻ መሪዎችንና ፊታውራሪዎችን አነጋግራለች፡፡ የተለያዩ የቤት ስራዎችን እንደወሰዱም ይታመናል፡፡

በዚሁ ዓመት ከባህር ማዶ ያፈተለከውና ለአገር ውስጥ መገናኛ ብዙሀንም የደረሰው ዜና የግንቦት ሰባቱ ሊ/መንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ከኤርትራ መንግስት በቀጥታ ያገኘውን የ500 ሺህ ዶላር እርዳታ መግለጹና ለምን ተግባር እንደሚውል ከፋፍሎ ማሳወቁ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ሌላውን እንተወውና በአገር ውስጥ ለሚገኘው የግሉ ፕሬስ የተመደበው መንቀሳቀሻ የፕሮፖጋንዳ ስራ ለማካሄድና የሕዝቡን ስነልቦና ለአመጽ ለማነሳሳት ስራና ለማሳተሚያ እንዲውል የተመደበው 200 ሽህ ዶላር ይገኛል፡፡ ይህም ወደ 1 ሚሊዮን 800 ሽህ ብር መሆኑ ነው፡፡ ይህ ገንዘብ በተለያየ መልኩ ወደ አንዳንድ የግል ጋዜጦችና መጽሔቶች ይደርሳል ተብሎ ታስቧል፡፡

ሕጋዊ የገንዘብ ልውውጥ መንገዶችን ባልተከተለ መልኩ በየትኛውም ዘዴ አገር ውስጥ ባሉ ወኪሎቻቸውም ይሁን ነጋዴዎች ወይንም ኤምባሲዎችና ዲፕሎማቶች በኩል ሊያገኙት እንደሚችሉ መጠራጠር አይገባም፡፡ ዋናው ግዳጅና ተልእኮ በተመረጡት የግል ሚዲያ ጋዜጦችና መጽሄቶች፡ ጸሐፊዎች ፡አማካኝነት መንግሥትን የማጥላላት፡በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት የማሳጣት፤ ስሜት ቆስቋሽ ሃሰተኛ ውዥንብር በመንዛት አንዳንድ የዋሆችን ምሬት ውስጥ መክተት፤ ለአመጽ ተቃውሞ እንዲዘጋጁ በተሳሳተ መንገድ መቀስቀስ ለአንዳንድ ወኪሎችና ጉዳይ አስፈጻሚዎች የተሰጠ የቤት ስራ ነው፡፡

የግሉ ፕሬስ ጋዜጠኞች ሕግን ተላልፈውም ቢሆን በሚጽፉትና በሚያሰራጩት ጉዳይ ሕጋዊ ተጠያቂነት ቢመጣ፤ ቢታሰሩ ሲፒጄና የመሳሰሉት ዓለም አቀፍ ተቋማት፤ እንዲሁም ሌሎች በመንግስት ላይ ቀጥተኛ ጫና ለማሳደር የሚችል እርምጃ እንደሚወስዱ፤ መታሰራቸው እነርሱ የሚፈልጉትን ቀን የሚያቃርብ መሆኑንና ለዚህም አንዳችም ፍርሃትና ጭንቀት ሊኖር እንደማይገባ፤ ጭምር ለማሳወቅ ተሞክሯል፡

ለዚህም የሚሆን በምዕራቡ መንግስታት ኤምባሲዎችና ውጭ ባሉ የጋዜጠኛ መብት ተከራካሪ ነን በሚሉ ድርጅቶች ቀጥተኛ እውቅናና ድጋፍ የሚሰጠው የጋዜጠኛ ማህበር (ወይንም) ፎረም በአስቸኳይ እንዲቋቋም እውቅና ባይሰጠውም ቢሰጠውም የጋዜጠኞችን መታሰር እየተከታተለ ወይንም በእስር ላይ ያሉት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ፤ ያለመሰልቸት ድምጹን እንዲያሰማ፤ የተወሰኑት ቢታሰሩ እንኳን ሂደቱና አሰራሩ እንዳይስተጓጎል በሌሎች እንዲቀጥል የግንቦት ሰባት አመራርና ሌሎችም መክረውበታል፡፡

ይህ የግሉ ፕሬስ የሚያደርገው በከፍተኛ ገንዘብ የተገዛ የቀጣዩ ምርጫ ቅስቀሳ ቅድመ ዝግጅት ከተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ተቀናጅቶ ለእነሱም ጠንካራ ድምጽ ሆኖ ልክ እንደ 97ቱ ግንባር ቀደም ሚና እንዲጫወት፤ ማንኛውንም መስዋትነት ለመቀበል እስርና እንግልት እንዳይፈራ ዝግጁ ሆኖ በድፍረት እንዲጋፈጥ ቀጭን ትእዛዝና መመሪያ ወርዶለታል ከኢሳት አለቆቹ ፡፡ ለዚህም በተግባር እየተንቀሳቀሰ ሲሆን፣ የመነሻ ዓላማው ያደረገው በጽንፈኛው ዲያስፖራና

ትዕዛዙን የተቀበሉትም ትላንት የኢትዮጵ ጋዜጣ ባለቤትና አሳታሚ ዛሬ ደግሞ የኢሳት አዘጋጅ ከሆነው ግለሰብ ነው፡፡ የትላንቶቹ ስመ ብዙ ጋዜጦች በየራሳቸው ምክንያቶች በገበያው ላይ ባይኖሩም ዛሬ ስማቸው ተቀይሮ በመጽሔት ደረጃ አድገው ግን ደግሞ የትላንቱን ስራ እየሰሩ በተግባርም እየደገሙት ይገኛሉ፡፡

ባለቀለም ሽፋን መጽሄቶች ትላንት በፍቅርና በማህበራዊ ጉዳይ ብቻ ለመስራት ፈቃድ የወሰዱት በርካታ መጽሄቶች ዛሬ ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ ተለውጠው የፖለቲካ መጽሄቶች ሆነዋል፡፡ የሚሸጡትም 10 ብርና ከዚያም ያልፋል፡፡ ትላንት አይደለም አንድ መጽሄት በሳምንት ማሳተም አንድ ጋዜጣም ለማሳተም ምን ያህል የገንዘብ ችግር እንደነበር የሚያውቁት ይናገራሉ፡፡ እዚህ ላይ አንድ ልብ ሊባልልኝ የሚገባው የግሉ ፕሬስ በቁጥርና በዓይነት ለምን አደገ፣በዛ ለማለት አይደለም። ይህ እንዲሆንማ ሕገመንግሥቱም ዋስትና ሰጥቷል፣ መንግሥትም ይህንኑ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። በመሆኑም ሕዝቡ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተሻለ የሚዲያ አማራጭ እንዲኖረው የግሉ ሚዲያ እንዲያብብና እንዲጠናከር ከልብ ከሚፈልጉት መካከል አንዱ መሆኔን ላረጋግጥ እወዳለሁ።

ይሁን እንጂ የግሉ ፕሬስ ሲጀመር እንደነበሩት የመጀመሪያዎቹ ብዙዎች ጋዜጦች; አሰስ ገሰሱን ወሬ እየያዙ ፖለቲካውን የሚያቦኩትና የሚጋግሩት፤ ያሻቸውን ወገንተኛና በጥላቻ የተሞላ አቋም፤የግለሰቦችን በሕግ የተከበረ መብትና ስብዕና ጭምር በማጠልሸትና ማህበራዊ ተቀባይነትን ለማሳጣት፤የሀሳብ ልዩነትን በማውገዝና ሁሉም በአንድ አቅጣጫ ብቻ እንዲያስብና እንዲተም፤ ከዚያ ውጭ ሄዶ ያሰበ፣ የተናገረና አቋም የያዘ አንዱን "የማርያም ጠላት፣" ሌላውንም "የሰይጣን ወዳጅ" በሚል ንጹሃን ዜጎችን ሲፈርጁ እንደነበር ይታወሳል። ማህበራዊና የፍቅር ርዕሰ ጉዳዮችን ከፖለቲካ አደባልቀው፣ፍቅር አይሉት ፖለቲካ፣ማህበራዊ አይሉት ኢኮኖሚ፣ በዘይት ላይ ውሃ ከልብሰው- ነገሩ ሁሉ ዘይት አንለው- ውሃ፣ ውሃ አንለው-ዘይት ሆኖብን ቅጣምባሩ እስኪጠፋን ሲያደናቁሩንና በፕሬስ ስም ሲነግዱብን ኖሩ።

ታዲያ አሁንም የተላያዬ ሥም ይዘው ወደ ገበያው ብቅ ብቅ ያሉት አንዳንድ የግል ፕሬሶች ይዘታቸውና እያንጸባረቁት ያልው አመለካከት በ90ናዎቹ መጀመሪያና

አጋማሽ የነበሩ አንዳንድ ፕሬሶችን ዓይነት ሽታ የያዙ ናቸው። ቁጥራቸው የበዛ የግል ፕሬሶች እያሉና እንዳሻቸው እየጻፉም ጭምር የፕሬስ ነጻነት የለም ይላሉ። አንዳንዶቹ ምንም ዓይነት የማስታወቂያ ሽያጭ ሳይኖራቸው የማሳተሚያ ገንዘብ አቅሙን ከየት አገኙት? የቤት ኪራይ፤ የሰራተኛ ደመወዝ፤የተጨማሪ ጽሁፎች ወይም የ"አምደኞች" ክፍያና ሌሎች ተያያዥ ወጭዎችን በመሸፈን ትርፋማ ሆነው በገበያው ሊዘልቁ እንደሚችሉ በእርግጥም አጠያያቂ ነው የሚሆነው።

ከዚህ ሁሉና ከእያንዳንዱ በስተጀርባ ያለው ተዋናይ ማነው የሚለው ጥያቄ ሲነሳ ግልጽና የማያሻማ ሊያስተባብሉት የማይችሉት እውነት ላይ ያደርሰናል፡፡ ሰዎቹ የመደቡት ብቻ ሳይሆን ከመደቡትም በላይ ገንዘብ በተለያየ መንገድ ለስራ ማስኬጃ ገብቷል፣ እየገባም ነው የሚል ከራሳቸው ጓዳ ያፈተለኩ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ፕሬሶች ሥራ ማስኬጃቸውንና ወጭአቸውን በራሳቸው ሸፍነውና ነጻ ሆነው ካልተንቀሳቀሱ በስፖንሰሮቻቸውና በገንዘብ እየደጎሙ ለሚያሰሯቸው አካላት ፍላጎት ብቻ በመንበርከክ በእነሱ ተጽእኖ ሥር መውደቃቸው አያጠያይቅም። ይህም ከትክክለኛው መንገድና ከተቋቋሙበት ሙያዊና ሥነ ምግባራዊ መርሆ ውጭ እንዲሆኑ ስለሚያደርጋቸው ተቀባይነታቸውን በመሸርሸር ሕልውናቸውን የሚገዳደር ይሆናል። ስለዚህም እንደነዚህ ዓይነቶቹ ፕሬሶች ሚዛናዊ፤ ተአማኒ፤ ወገንተኛ ያልሆነ፤ የሁሉንም አስተያየትና አመለካከት በእኩልነት በማስተናገድ ተጨባጭ መረጃ ሚያቀርብ አስተማሪና አዝናኝ ከመሆን ይልቅ በአንድ ወገን ጥላቻ ተሞልቶ እንደ ጋሪ ፈረስ በልጓም የሚመራ ዓይነት ይሆንና አደጋውና አወዳደቁ የከፋ ይሆናል።

በሰላም ውስጥ እንጂ በደፈረሰ ሰላምና በሁከት ውስጥ ነግዶ ማትረፍ አይቻልም።፡ በሃገርና በወገን ኪሳራ ለማትረፍ ሁከትን ለምን እንደሚናፍቁት ግር ያሰኛል፡፡ እነርሱ ግን ይህንን በነሱ ቋንቋ "የሕዝብ ፍቅር፤ለሃገር ማሰብ፣የፕሬስ ነጻነት ናፍቆት" ወዘተ ይሉታል ፡፡ እውነቱ ግን ለገንዘብ ፍቅር ተገዝተው በመሳሪያነት መስራታቸው ነው፡፡ የተጸናወታቸው የትርምስ፣ የሁከትና የጦር አውርድ ዛር "ግፉ በለው፣ አለበለዚያም ይገፋል በግዱ" ያሰኛቸዋል፡፡ የእስክንድር ነጋና የሲሳይ አጌና ማደጎዎች የጌቶቻቸውን አደራ አጥብቀው ይዘው ገፍተውበታል፡፡ ደግሞም 97ን በቀጣዩ ምርጫ እንደግማለን ብለው ቃል ገብተዋል፡፡ በድርጅትም በሰንቅም፤

ከባህርማዶ እስከ አገር ውስጥ እየታገዙ እየተደገፉ የቤት ስራቸውን ተግተው እየሰሩ ነው፡፡

ከሕትመቶች ጀርባ የቀድሞዎቹ ተዋናዮች ራሳቸውን ሕቡዕ እንደገቡ ቆጥረው በብዕር ስም በየመጸሄቱ ውጊያቸውን ቀጥለዋል፡፡ ትክክለኛውን ሙያዊና ሥነ ምግባራዊ የጋዜጠኝነት ግዴታ ከመወጣት ይልቅ የኢሳትና የሌሎች ጣልቃ ገብ ኃይሎች ሪፖርተሮችና የመረጃ ምንጭ በመሆን የሎሌነት ሥራቸውን ተግተው ለመቀጠል ደፋ ቀና ሲሉ ይታያሉ፡፡ ከውስጥ አዋቂዎች እንደተገኘ መረጃ ከሆነ አንዳንድ ወኪሎቻቸው በወር እሰከ 700 ዶላር ያገኛሉ ይባላል፡፡ የስልክ፤ የትራንስፖርት ወጪ፤ የሆቴልና ሌሎች ወጭዎች በሚልም ከነመጠባበቂያ ወጭው ተሰልቶ ይደርሳቸዋል፡፡ ዋናው ተግባር በየትኛውም ጽሁፍና መጣጥፍ በወግና በቀልድ ብጤም በስርዓቱ ላይ የመረረ ጥላቻን የሚያሳድሩ መልእክቶቻቸውንና "ምርጥ ሰማይ ጠቀስ አሉባልታዎችን" በጠጠሩና "እንባ አመንጭ" አገላለጽ ወይም ሆድ በሚያስብሱ "የተከሸኑ ቃላት" ለሕዝብ ማድረስና ማሰራጨት ነው፡፡ ይች ናት እንግዲህ አሪፍ የጋዜጠኝነት ሙያና ሥነምግባር!! ልክ እንደ 97ቱ ዓይነት ‹‹የሱናሜ ማዕበል›› አጋጣሚ በድንገት ተነስቶ ሕዝብ ይደግፈናል ብለው የተስፋ ዳቦ ጋግረዋል፡፡ እውነታውን በውል ተረድተው በትክክለኛው መንገድ መራመድ ሲችሉ ዓላማቸውን በሁከትና በትርምስ በተለይም በጋዜጠኝነት ሽፋን ለማሳካት መንቀሳቀሳቸው በእጅጉ አሳዛኝ ነው።

ደጋግመው የሚያነሱትን የፕሬስ ፤ የመናገር፤ የዲሞክራሲ፤ የመደራጀት፤መብትና ነጻነት ወዘተ የጋዜጣ ማሻሻጫና የሕዝብ ቀልብ መሳቢያ እንጂ ስብዕናቸው ከዚህ እጅግ ተቃራኒ ነው፡፡ ፍጹም አምባገነን፤ ርህራሄም የሌላቸው ጨካኞች ናቸው፡፡ እድሉን ቢያገኙ ምንም ከማድረግ አይቆጠቡም፡፡ ከእነሱ አስተሳሰብና አመለካከት ወይንም ድርጅት ውጪ ማንንም ማየትም፤ መስማትም፤ መቀበልም፤ ማስተናገድም የማይፈቅዱ አቅም ካገኙም ከማስወገድ ከማጥፋት የማይመለሱ ናቸው፡፡ የተቃዋሚውና የግሉ ፕሬስ ቁርኝት በብዙ ድርና ማግ የተሳሰረ ነው፡፡ በየትኛው መስፈርት ዲሞክራቶች፣ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ፤ የፕሬስ ነጻነት ተሟጋች፤ የነጻነት አርበኛ ሊሆኑ እንደሚችሉ "ለማያውቅሽ ታጠኝ" ነውና ነገሩ ከወዲሁ ሰልፋችሁን አስተካክሉ የሚለው የግል ምክሬ ነው።

አሁን አሁንማ በግጥም ምሽቶችና በመጽሀፍት ምረቃ ዝግጅቶች ወዘተ .... ስም በመሰባሰብ ውግዘት ኩነና ሕገመንግሥታዊ ስርዓቱን ማጠልሸት እንደ አዲስ ፋሽን ተይዟል፡፡ ዋናው መልእክቱን እንደ ግሉ ፕሬስ ሁሉ ለሕዝብ ማድረስ ነው፡፡ በጎዎችንና ታላላቅ ሀገራዊና ህዝባዊ ጠቀሜታና ፋይዳ ያላቸውን ስራዎች ማጥላላት፣ ማናናቅ፣ ማዋደቅ፣ የግለሰቦችን ስብእና ማቆሸሽ፤ማዋረድ፣ በስማ በለው የስም ማጥፋት ዘመቻ ማካሄድ፤ በጭፍንነትና በስሜታዊነት መጋለብ፤ ሰክኖ አለማሰብና አለማስተዋል፤ በጀብደኝነት ለጥፋትና ለውድመት መክለፍለፍ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲከኞችና የአንዳንድ የግሉ ፕሬስ አይነተኛ መለያ ሆኖ እስከመቼ እንደሚዘልቅ አይታወቅም፡፡፡፡

በዚህ እብደትና በእኔ እበልጥ እኔ አበልጥ የመናናቅና የመጠፋፋት ልክፍት ውስጥ የእዚህች ታላቅ ሀገር ሕዝብና የወደፊቱ ትውልድ እጣፈንታ ወደየት ሊያመራ ይችላል? የሚለው ለእነርሱ የሚያሳስባቸው አይደለም። እኛ የምንፈልገው ካልሆነ የፈለገው ደም ይፍሰስ፤ የፈለገው ሰው ይለቅ፤ እሳተ ገሞራ ይውረድ፤ ሀገር ሕዝብ ሰላም የሚባለውን አናውቅም የሚሉ አምባገነኖች፤ እንዴት የፕሬስ ነጻነትና የዲሞክራሲ ተሚጋችና ጀግኖች ተብለው እንደሚወደሱ አስደናቂ ነው የሚሆነው፡፡ ከሁሉም አሳፋሪውም ይሄ ነው፡፡ 97 ዓ.ምን በመናፈቅ የሚደረገው የአብዛኛው የግሉ ፕሬስ ዝግጅት ዳር የማያደርስ፤ በታሪካዊ ስህተት የተሞላ፣ የውድቀት ጉዞ እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ህዝብ ሀገሩንም ሰላሙንም እድገቱንም አጥብቆ ይጠብቃል፡፡ለሁከትና ብጥብጥ ግዜም ቦታም የለውም፡፡